# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጥር 7 ቀን 2003 ዓ.ም**

- **ከአፍሪካ ትልቁ የገበያ ማዕከል መርካቶ ሲተራመስ ሰነበተ፤**
  **ህዝቡ እቃ አጥቶ ባዶ እጁን ተመለሰ፤**
- **የወያኔ ባለስልጣናት ገጠር ገበያዎች ድረስ በቡድን ተሰማርተው**
  **በህዝብ ገንዘብ እህል መሰብሰብ ጀመሩ፤**
- **ታቆሽሻላችሁ የተባሉ ዜጎች ታፍሰው ተወሰዱ፤**

የወያኔ ቡድን ለማስመሰል እና ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲል ብቻ ያለ በቂ ጥናት እና ውይይት በነሲብ የዋጋ ተመን አወጣሁ ቢልም በሸማቹና በነጋዴው መሀከል ከፍተኛ ትርምስ መፈጠሩ ታወቀ።

ሐሙስ ታህሳስ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በመለስ ዜናዊ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ አሉ የተባሉ 580 የሀገሪቱን ቱባ ነጋዴዎች እያነጋገረ ባለበት ወቅት አስቀድሞ ባልተዘጋጀና ባልተጠናበት ሁኔታ ድንገት የዋጋ ተመን አወጣሁ ብሎ የሸማቹን ማህበረሰብ ድጋፍ ለማግኘት ያደረገ ቢሆንም የሚቀድመውንና ለህዝቡ መሰረታዊ የተባሉትን ወደ ጎን ትቶ በቅንጦት እቃዎች ላይ ዋጋ ከመተመኑም በተጨማሪ የነጋዴውንም ችግር ያላገናዘበ በቂም እና በጥላቻ ላይ የተመሰረተ እርምጃ መውሰዱ እያነጋገረ ይገኛሉ።

በሀገሪቱ ውስጥ ነባር እና ወሳኝ ናቸው የተባሉት ነጋዴዎችን አወያየሁ ለማለት ያህል በቢሮው መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ለአንድ ቀን ያዋላቸው ቢሆንም አንድም የረባ ስምምነት ሳያደርጉ ይልቁንም ነጋዴዎቹ እሮሮና ምሬት ሲያሰሙ መለስም አንዴ ሲለማመጥ ሌላ ግዜ ሲያስፈራራና ሲያስጠነቅቅ እንደዋሉም ታውቆዋል።

የህዝቡ መሰረታዊ ፍጆታ የተባሉት እህልና ጥራጥሬዎች እንዲሁም የጉዋሮ አትክልቶች ላይ በቂ ጥናት ተደርጎ የወቅቱን ሁኔታ ያገናዘበ የዋጋ ተመን ማውጣት ሲገባው ለህዝቡ እዚህ ግባ የሚባል ፍላጎት እና ከአቅሙ ጋር ያልተገናዘቡትን እነ ቢራና  ስጋ ዋጋ የተመነላቸው መሆኑ የሚያሳዝን እና በህዝቡ ላይ መቀለድ መሆኑን በብስጭት ነዋሪዎች እየተናገሩ ይገኛሉ::

በሀገር ውስጥ የሚመረተውን ስኩዋር በ14 ብር እንዲሸጥ ዋጋ የተመነው ወያኔ ነጋዴዎች ከፋብሪካው ላይ ቀጥታ ገዝተው ለቸርቻሪዎች እንዳያከፋፍሉ እራሱ ባቁዋቁዋመው የገንዘብ መዝረፊያ ድርጅት አማካኝነት ብቻ እንዲሸጥ በማድረጉ የአንድ ኩንታል ዋጋ 1300 ብር እንዲሆን አድርጎ የትራንስፖርት እና የማስጫኛና የማስወረጃ ሂሳብ ሲደማመር ከ1500 ብር በላይ እንደሚያሻቅብ እያወቀ ሆን ብሎ ነጋዴውን ከሸማቹ ለማጋጨት ያደረገው ተንኮል እንደሆነ በይፋ ተረጋግጦዋል::

በመርካቶ ውስጥ ሱቅ ያላቸው ቸርቻሪ ነጋዴዎች በወጣው የወጋ ተመን በመደናገጥ እንዲስተካከልላቸው አቤቱታ ለማቅረብ  ወደ የክፍለ ከተማው ንግድ ቢሮ ቢሔዱም ሰሚ ካለማግኘ ታቸውም በተጨማሪ ሱቃችሁን የዘጋችሁት አድማ ለመምታት እና አመፅ ለመቀስቀስ ነው በማለት ከፍ ያለ የገንዘብ ቅጣት እንደተጣለባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

አስቀድሞ በከፍተኛ ገንዘብ ለቸርቻሪዎቹ ያከፋፈሉትን ትላልቅ ነጋዴዎች ዋጋ እንዲቀንሱ ሳይደረግ በውድ ዋጋ ያስገቡት ቸርቻሪዎች ላይ ድንገተኛ እርምጃ መወሰዱ አግባብነት የጎደለው በቂም እና በጥላቻ ቤተሰቦቻቸው እንዲበተኑ ሆን ተብሎ የተደረገ ሴራ ነው ሲሉም ነጋዴዎቹ እያነቡ ሲገልፁ ተደምጠዋል::

የሀገር ውስጥ ምርት የሆነው ስኩዋር ከፋብሪካ ሲወጣ በ4 ብር መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ወያኔ ከአንድ ኩንታል ከዘጠኝ መቶ ብር በላይ ትርፍ እያግበሰበሰ 1300 ብር እየሸጠ እሱ የበላውን ገንዘብ ነጋዴና ሸማቹ እንዲከፍል ማድረጉ ቀጥተኛ ስግብግብነቱን ያሳያል ያሉት ነጋዴዎቹ አሁንም  በግዴታ 14 ብር  እንዲሸጥ ተብሎ ዋጋ መተመኑ ሁኔታዎችን ያላገናዘበ መሆኑን  ይገልፃሉ::

ጊዜ ተወስዶበት እና አስቀድሞ በበቂ ሁኔታ ጥናት ሳይደረግበት ድንገት ለራሱ ፖለቲካ መጠቀሚያ  ሲል ብቻ የዋጋ ተመን ያወጣው የወያኔ መሰሪና መርዘኛ ቡድን ህዝቡ በነጋዴው ላይ ጥላቻ እንዲያተርፍ ነጋዴው ደግሞ በሸማቹ ላይ ቂም እንዲቁዋጥር እና እርስ በርስ እንዲከፋፈሉ አልፎ ተርፎ በጎሪጥ እንዲተያዩ ሆን ብሎ ያደረገው መሆኑን ህዝቡም ነጋዴውም በማወቃቸው ያሰበው ተንኮል መልሶ ወደራሱ በመዞሩ መያዣ እና መጨበጫ አጥቶ እርስ በርስ አስፈጻሚ የተባሉት ባለስልጣናት እየተወዛገቡ እንደሚገኙ ታውቆዋል::

አከፋፋዮች እና ጅምላ ሻጭ ነጋዴዎች ከውጭ ሀገር ገዝተው ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡበት የእቃዎች ዋጋ በጉምሩክ በኩል በግልጽ እየታወቀ ለዓመታት ህዝቡ ሲዘረፍ አንዳችም እርምጃ ሳይወስድ ኖሮ ዛሬ ህዝቡ ትዕግስቱ አልቆ በራሱ ግዜ ፊቱን ወደ ወያኔ ባዞረበት ወቅት ድንገት ለማምለጫ እንዲሆነው የዋጋ ተመን ቢያወጣም ከፍተኛ ትርምስ እና ውዥንብር ተፈጥሮ ይገኛል::

አንድ ሊትር ዘይት ከ13 ብር በታች ከኢንዶኔዥያና ከሌሎች ሀገራት ተጭኖ መግባቱን የሚያውቁት የወያኔ ባለስልጣናት ሀገር ውስጥ ለህዝቡ 35 እና 40 ብር ሲሸጥ ዝም ከማለታቸው በተጨማሪ ቫት ብቻ ይሰብሰብ እያሉ ከሀብታም ነጋዴዎች ጋር ተመሳጥረው ከርመው ዛሬ እንደማያውቁ ሆነው መልሰው በነጋዴው ላይ ጣታቸውን መቀሰራቸው የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር ወራዳ ተግባር ነው የሚሉ ምሁራኖች ቁጥራቸው የበዛ ነው::

የዋጋ ተመኑ ከወጣ በሁዋላ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም እና ትልቁ የገበያ ማዕከል የሆነው መርካቶ ምስቅልቅሉ ወጥቶ አንደኛው ሱቅ ተዘግቶ ሌላው ተከፍቶ እቃዎች እጥረት ተፈጥረው እንዲያውም የለም የሚል ምላሽ በዝቶ ህዝቡ ሲንከራተት እና ባዶ እጁን ወደ ቤቱ ሲመለስ ነው የሰነበተው::

ለሸማቹ ሲባል ተወሰደ የተባለው እርምጃን ተግባራዊ ባላደረጉ ነጋዴዎች ላይ የእስር እና የገንዘብ ቅጣት እየተጣለባቸው ቢሆንም አሁንም የወያኔ የበኩር ልጆች የሆኑ ነጋዴዎች ግን ከተፈቀደው የዋጋ ተመን በላይ ሲሸጡ እያዩ አንዳችም እርምጃ ሳይወሰድባቸው ይልቁንም ከለላና ሽፋን ሲሰጣቸው እየተስተዋሉ ናቸው::

በአንድ ሀገር ሁለት አይነት ነጋዴዎችን የፈጠረው ወያኔ እራሴ የፈጠርኩዋቸው የሚላቸው ከትግል በሁዋላ ወደ ንግዱ ዓለም እንዲገቡ የተደረጉና ዛሬ አስመጪና አከፋፋይ ለመሆን የበቁት ቱባ ነጋዴዎች ያስመጡትን እቃ በየመጋዘኖቻቸው እያስቀመጡ የለም በማለት ቸርቻሪ ነገጋዴዎችን ባዶ እጃቸውን እንዲመለሱ ሲያደርጉ አንዳችም እርምጃ ሳይወሰድባቸው በራሳቸው ጥረት ጥረው ግረው ለትልቅ ደረጃ የበቁትን ነጋዴዎች ግን ባልሰሩት ስራ እና ባላጠፉት ጥፋት አንጴ መጋዘኖቻቸውን ሲያሽጉ ሌላ ግዜ ፖሊስ ጣቢያ እየወሰዱ ሲያስፈራሩዋቸው የሰነበቱ መሆኑ ታውቆዋል::

ሌላው ቀርቶ በአዲስ አበባ ከተማ ከአንድ ወር በፊት የአትክልት ነጋዴዎችን እያስፈራሩ እና እያሰሩ ብሎም ሱቆቻቸውን እያሽጉባቸው የነበሩትን ነጋዴዎች ህንፃ ሊሰራ ነው በሚል ሽፋን ሱቆቻቸው እቃ እንደያዙ በቡልዶዘር አፍርሰው ያባረሩዋቸው ሲሆን አሁን ደግሞ ሙዝ፣ ፍራፍሬዎችን እና አትክልቶችን በቀጥታ ከአምራቹ የሚረከቡና ለሸማቹ የሚያቀርቡ የወያኔ ሰዎችን እያደራጁ በመሆኑ ብዙ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩና ለብዙ ዓመታት በዚሁ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ያሉት ነጋዴዎች ከፍተኛ አደጋ ውስጥ እየወደቁ መሆኑን ከወዲሁ ነጋዴዎቹ ስጋታቸውን እየገለፁ ናቸው::

የአርባ ምንጭ ሙዝ አምራች ማህበር በሚልም የገበሬ ካድሬዎችን አደራጅተው በቅርቡ ሙሉ ለሙሉ ገበያውን እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ በአዲስ አበባ የተለያዩ ቦታ መጋዘኖች ተሰጥተዋቸው እራሳቸው አምጥተው ለህዝቡ በቀጥታ ለመሸጥ እንዲችሉ እየተዘጋጀላቸው ሲሆን ከአምራቹ ተቀብለው የሚቸረችሩ የነበሩ ነጋዴዎችን ከጨዋታ ውጭ ሊያደርጉዋቸው መሆኑም ታውቆዋል::

በእህልና ጥራጥሬ ላይ የዋጋ ተመን እንዲወጣና ከገበሬው እና ከሸማቹ መሀከል ያሉ ስግብግብ ወያኔ ሰራሽ ነጋዴዎች እንዲወገዱ ህዝቡ ቢጠይቅም ዋጋው የተረጋጋ በመሆኑ ለግዜው ተመን አያስፈልገውም በሚል የህዝቡን ጥያቄ ውድቅ አድርገውታል::በአንጻሩ ባለስልጣናቱ

የዓመት የእህል ፍጆታቸውን መኪና ከየመስሪያ ቤቶች አስልከው በጎጃም ገጠር ገበያዎች ውስጥ ሳይቀር አሰማርተው ጤፍ እየሰበሰቡ  ይገኛሉ።

የመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች በበኩላቸው ገንዘብ ጭምር ከመስሪያ ቤቱ ወጪ አድርገው ለአንድ ከፍተኛ መኮንን 12 ኩንታል ጤፍ ተገዝቶ እንዲመጣ ወደ ተለያዩ ጤፍ አምራች በሆኑ ከተሞች ልከው እየሰበሰቡ ባለበት በአሁኑ ወቅት ጤፍ እና መሰረታዊ የሆኑ የሸሮ እህሎች ላይ ዋጋ ተመን ይውጣልን ብሎ ህዝቡ ያቀረበውን ጥያቄ ወደ ጎን አድርገው በስጋና በቢራ ብሎም በውስኪ ላይ የዋጋ ተመን አወጣን ብለው መጨፈራቸው የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን ነው እያለ ህዝቡ ወያኔን እያማረረ ይገኛል።

መላው የጠፋበት መለስ ዜናዊ እና ቡድኑ ከውጭ ሀገር ለእረፍት የመጡትን ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች በየሰፈር ካድሬዎች አማካኝነት የመጥሪያ ደብዳቤ ተበትኖ በያዝነው  ጥር ወር እንዲሰበሰቡ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ደብዳቤው የደረሳቸው ብዙዎቹ ግን የመጡበትን ጉዳይ ሳይፈጽሙና  የእረፍት ግዜያቸውን ሳይጠቀሙ በጥላቻ ሀገር ጥለው  እየወጡ መሆኑም ታውቆዋል።

በዚህ በያዝነው ወር ውስጥ መለስ ዜናዊ ጋር ይወያያሉ ተብሎ የተበተነው ደብዳቤ ላይ እንደሰፈረው ከሆነ በሀገር ውስጥ ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ የተፈጠረላቸው መሆኑን ተገንዝበው ፊታቸውን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲያዞሩ  ሊለማመጥ መሆኑ ተገልጾዋል።

በተያያዘ ዜና ከነጋዴዎች በላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት በሀገሪቱ እንዲጠዝ እየሰራ ያለው ወያኔ ሰሞኑንም በድጋሚ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ በማድረግ በእሳት ላይ ቤንዚን እያርከፈከፈ በህዝቡ ላይ እየተጫወተ ይገኛል።

የኑሮ ውድነት እንዲጠዝ ነጋዴዎች ግንባር ቀደም ተዋናይ ናቸው  እያለ የሚደነፋው ወያኔ መቆሚያ በሌለው የነዳጅ ዋጋ ህዝቡን በከፍተኛ ሁኔታ እያስቃየ መልሶ ጣቱን በነጋዴዎቹ ላይ እየቀሰረ  መሆኑም ታውቆዋል።

የዓለም ነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ሳያሳይ ባለበት እየረገጠ ቢሆንም የወያኔ ቡድን ግን ከመቀነስ እና ከማረጋጋት ይልቅ በህዝቡ ቁስል እንጨት እየሰደደ እና የኑሮ ውድነቱን እያባባሰ ህዝቡ ከአቅሙ በላይ እንዲሆን እየሰራ መሆኑም ተረጋግጦዋል።

ሰሞኑን በተደረገው የዋጋ ጭማሪ መሰረት የአንድ ሊትር ቤንዚን ዋጋ 15 ብር ከ55 የነበረው 16 ብር ከ55 ሆኖ የ1ብር ጭማሪ ሲደረግበት ናፍጣ 13 ብር ከ24 ሳንቲም የነበረው አሁን 13 ብር ከ95 ሆኖ የ71 ሳንቲም ጭማሪ እንዲሁም የቤት መጠቀሚያ እና የህዝቡ መሰረታዊ ፍጆታ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው ጋዝ 11 ብር ከ75 ሳንቲም የነበረው አሁን 12 ብር ከ36 ሆኖ የ61 ሳንቲም ጭማሪ ከማሳየቱም ጋር በተያያዘ  የትራንስፖርት ዋጋም ጭማሪ መደረጉ ታውቆዋል።

የዕለት ጉርስ መቅመስ እያቃተው ኑሮው እያሳሰበው የመጣው መላ የሀገሪቱ ህዝብ ወዳጅ ዘመዶቹን እንዳይጠይቅ የትራንስፖርት ዋጋው እየናረ በመምጣቱ ሊከፍለው ከሚችለው በላይ

በመሆኑ ተቆራርጦ ለችግር ግዜም መጠያየቅ ማቆሙ የታወቀ ሲሆን በታክሲ ከ10 ሳንቲም እስከ 35 ሳንቲም በሀገር አቋዋራጭ ከ2 ብር እስከ 10 ብር ድረስ ጭማሪ ተደርጎዋል::

በሌላ ዜና የወያኔው ቡድን በዘረጋው ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው ምክንያት የትውልድ ቀዬአቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ያደረጋቸውን አርሶ አደሮች እና ወጣቱም እናት አባቱን ጥሎ ወጥቶ ለጎዳና ህይወት ተዳርጎ ለዓመታት ኑሮ ብሎ የጀመረ ቢሆንም ሰሞኑን በድንገት ከተኙበት እያፈሰ ወደ ጦር ካምፕ እያጉዋጉዋዘ መሆኑ ተመለከተ::

ገበሬውን ከግብርና እፈናቀለ ለልመና እየዳረገ....... ወጣቱን ትውልድ በማይረባ የትምህርት ፖሊሲው እንዲደናቀፍ እያደረገ አልፎ ተርፎ ትውልድ ገዳይ በሆኑ መርዛማ ሱሶች እንዲጠመዱ እያደረገ ወደ ጎዳና ህይወት እያስወጣ ያለው ወያኔ ዛሬ ከተማ አቆሸሻችሁ በሚል ተጠይፎ ማክሰኞ ጥር 3 እና ረቡዕ ጥር 4 ቀን 2003 ዓ.ም ከአዲስ አበባ እያፈሰ ወደ ፍቼ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ማጎሩ ታውቆዋል::

በመልሶ ማልማት ስም ለዘመናት ከኖሩበት ቤት እያፈናቀለ ለጎዳና ህይወት የዳረጋቸውን ዜጎች ጨምሮ በተለያዩ ወያኔ ሰራሽ መሰሪ ተግባሮች ወደ አዲስ አበባ ጎዳና ህይወት የወጡትን ዜጎች ከተማ ታቆሸሻላችሁ በሚል ሰሞኑን ርሀብ የእለት ጉርሴ..... ድንጋይ ትራሴ..... ላስቲክ ብርድ ልብሴ .......ብለው በተኙበት ድንገት ሌሊት በመከላከያ ወታደሮች እና በወታደራዊ መኪኖች አስገድዶ እያፈሰ ወደ ፍቼ የጦር ካምፕ ከማጎሩም በተጨማሪ ግቢ ሲገቡ ሁሉም ፀጉራቸውን እንዲላጩ መደረጋቸው ታውቆዋል::

ከአዲስ አበባ 110 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው የጦር ካምፕ ውስጥ የታጎሩት እነዚህ በችጋር እና በብርድ የተጠበሱ ዜጎች ሌሊት እየታፈሱ ሲወሰዱ አንሔድም ችግራችንን ከህዝባችን ጋር ሆነን እንወጣልን ብለው ያንገራገሩ እና የተከራከሩ ወጣቶችን ብሎም አዛውንቶችን በመሳሪያ ሰደፍ እየደበደቡ እያስገደዱ ከመጫናቸው በተጨማሪ ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሱባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

የችግሩ መንስኤ እራሱ የወያኔ ቡድን መሆኑ እየታወቀ አውቆ እንዳላወቀ አይቶ እንዳላየ በመሆን አድገናል ሁለት ዲጅት አሀዝ እድገት አስመዝግበናል እያለ ጡሩምባውን እየነፋ ባለበት ወቅት ለተለያዩ ስራ የሚመጡ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች በካሜራ ጭምር በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ የጎዳና ተዳዳሪዎች መኖራቸውን በማስረጃ በመያዛቸው ውሸቱ የተጋለጠበት ይሄው አረመኔ ቡድን ዜጎችን ለችግር እና ለመከራ ከመዳረጉም በተጨማሪ ከተማ ታቆሸሻላችሁ እያለ እያፈሰ ከመውሰዱም በላይ በመሳሪያ ሰደፍ እየቀጠቀጠ እና እያሰቃየ መውሰዱ የሚያሳዝን እና የሚያንገበግብ በዜጎች ላይ እየተጫወተ መሆኑን በግልጽ ያሳየ መሆኑ ተረጋግጦዋል::

በሁለት ቀናት ውስጥ ብቻ ታፍሰው የተወሰዱት የጎዳና ተዳዳሪዎች ከ6 ሺህ በላይ እንደሆነ የጠቆሙት ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች በካምፑ ውስጥ የተለያየ ስልጠና እንሰጣችሁዋለን ይባሉ እንጂ ለጥቂት ግዜ አቆይቶ ደርግ ከየጎዳና ላይ እያፈሰ ቦዘኔ የሚል ታፔላ እየለጠፈ ወደ ተለያዩ በረሀዎች እንደበተናቸው ሁሉ ወያኔም የደርግን መንገድ ተከትሎ ከተማ ታቆሸሻላችሁ በሚል ያፈሳቸውን ዜጎች ወደ በረሀ ሊበትናቸው እንደሚችል ስጋታቸውን ገልፀዋል::

ትርፍ አምራች ገበሬ ነው እያለ የቃሊቲን ብረት እያቀለጠ ሜዳሊያ ሲሸልማቸው የነበሩ አርሶ አደሮች ለልመና ተዳርገው የጎዳና ህይወት ከጀመሩ ዓመታትን ያስቆጠሩትን ጨምሮ በቅርቡ በመልሶ ማልማት ስም በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ለብዙ ዓመታት ከኖሩበት ቀዬ እያፈናቀለ ያባረራቸውን ዜጎች መልሶ ከተማ ታቆሸሻላችሁ እያለ በጭነት መኪና እየጫነ በግዳጅ መመወሰዱ ሳያንስ መደብደቡ የሚያሳዝን እና የሚያንገበግብ ነው ተብሎዋል፡፡

ከካምፑ ውስጥ ጠፍተው እንዳይወጡ ዙሪያውን በወታደሮች እየተጠበቁ ከመሆኑም በላይ ተደብቆ ሊወጣ ያሰበ ቢኖር በጥይት ደረት ግንባሩን ተብሎ ሊገደል እንደሚችል ታፍሰው ሲገቡ መመሪያ እንደተሰጣቸው ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡